ዘላለማዊነት በፍልስፍና ሲመዘን

/ክፍል ፮/

□□□□

በፍልስፍናው ዓለም አንቱ ተብለው ታላቅ ከበሬታ እስከዛሬ ከሚቸራቸው ፈላስፎች አንዱ ፕሌቶ ነው ። " ከሞት በኋላ ሕይወት አለና ተፅናና " ቢሉት " እኔ ዘላለማዊ የምሆነው ገነት በመግባት ሳይሆን ምድር ላይ ትቼው በምሄደው ሥራዬ ነው " አለ ።

□□□

ብዙዎች ከሞት በኋላ ሕይወት " በመኖሩ " ይፅናናሉ ። አንዳንዶች ደግሞ የለም ዘላለማዊ ሕይወት ብሎ ነገር የለም ይላሉ ፤ እንዲያውም በእንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ ይሳለቃሉ ። ፊሮ የተባለው ፈላስፋ ደግሞ " እኔ የዘላለም ሕይወት ከሞትኩ በኋላ የማገኝ ከሆነ ውሻዬ ለምን ይቀርበታል? " ይላል " እንዲያውም በዘላለም ሕይወት መለኪያ ውሻዬ እንደ እኔ እያታልልም ፣ አይክድም ፣ አይሰርቅም ፣ አይዋሽም...ወዘተ..ስለዚህ ከእኔ ይልቅ በብዙ መመዘኛ ውሻዬ ለዘላለማዊ ሕይወት የተገባ ነው " ብሏል ።

□□□

ብ ዙዎቹ ፈላስፎች የዘላለም ሕይወት አሊያም ከሞት በኋላ ሕይወት የሚለው ሃሳብ መሠረቱ ሕንድ እንደሆነ ይናገራሉ ። ቱስካሮራ የተባሉ የሕንድ ጎሳዎች " አንድ ሰው ሲሞት ሟቹ መልካም ሰው ከሆነ ወደ አንድ የመንፈስ ዓለም ይወሰዳል ፤ በዚያም የአደን አውሬ ታድኖ የማያልቅበት ዓለም ውስጥ ይገባል " ሲሉ " ሟቹ ክፉ ከነበር ደግሞ ምግብ ከሌለበት እባብ ከሚርመሰመስበት ዓለም ውስጥ ይወድቃል " የሚል ነው እምነታቸው ።

⁞

ከዚያ ቀጥሎ ግብፆች ይነሳሉ ። ጥንታዊ ግብፃውያን እዚህ የምንኖርበት ቤት ወደፊት (ከሞት በኋላ) ከሚጠብቀን ቤት ጋር ሲነፃፀር እንደ ትንሽ ጎጆ ነው ይላሉ ። (ይኸ እንግዲህ አሁን በጎጆ ውስጥ የሚኖርን ሰው አይመለከትም) !

□□□

ከሞት በኋላ ሕይወት አለ የሚለው አስተሳሰብ ምንጭ ናቸው ተብለው የሚታመኑት ሕንዶች በሌላው የእምነት ክፍላቸው ደግሞ " ከሞትክ በኋላ ነፍስህ በሌላ ዓለም በድሎት ፣ ወይም በችግር ራሷን ችላ አትኖርም ፣ ነገር ግን እንደ ሰራኸው ሥራ በሌላ ፍጡር አካው ውስጥ ትገባለች እንጂ " ይላሉ ።...

ይቀጥላል...

@filsfina @filsfina

ዘላለማዊነት በፍልስፍና ሲመዘን

/ ክፍል ፪ /

□□□□

ይኽ እምነት ወደ ምዕራቡ ዓለምም ዘልቆ ከገባ ቆየትየት ብሏል ። ለዚህም ይመስላል ፓይታጎረስ አንድ ቀን በጣሊያን አውራ ጎዳና ሲሄድ አንድ አዛውንት ውሻቸውን በዱላ ሲቀጠቅጡ ተመልከቶ " በዚህ ውሻ ጩኸት ውስጥ የሚሰማኝ በቅርብ የሞተው ጓደኛዬ ድምፅ ነውና እባክዎ አይምቱት " በማለት ውሻውን ማስጣሉ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ የሚለው እምነት በተለየ መልኩ ወደ አውሮፓም እንደሰፋ ያሳየናል ።

□□□

ኒች ደግሞ " ከሞት በኋላ ሕይወት አለ የሚለው ነገር በምድራዊው ሕይወትህ በምትፈጥረው ምናብ የሚወሰን ነው " ይለናል ። " ለምሳሌም የእኛ የገሃነም እሳቤ ከእሳት ጋር የተያያዘበት ምክንያት አይሁዶች የበረሃውን ቃጠሎ አስከፊነት ስለኖሩበትና ስላለፉበት ከዚያ ጋር በማያያዝ ስለፃፉልን ነው ። በበረዶ መኖር ላንገሸገሸው ኤስኪሞ ግን ገሃነምን የእሳት ምሳሌ ብታደርግለት ምርጫው ያለጥርጥር እሱው ይሆናል " ይለናል ።

□□□

እንኳን ከሕይወት በኋላ ሌላ ሕይወት ለማሰብ የአሁን ሕይወትህ ራሱ ጥያቄ የሚገባው ነው የሚሉም አሉ ። ለዚህም ይመስላል ከጥንት ፈላስፎች አንዱ... " እኔ ራሴ አንድ ሰው ሆኜ አላውቅም ፤ ምክንያቱም አስቀድሞ እንደ ሕፃን ፤ ቀጥሎም እንደ ወጣት ፣ ከዚያም እንደጎልማሳ፣ በመጨረሻም እንደ ሽማግሌ ኖሬአለሁ ። ከሞት በኋላ ሕይወት ቢኖር እንኳ ዘላለማዊውን ሕይወት እንደማን ሆኜ ነው የምኖረው? " ይላል ። እንደገናም " እኔ የሕይወት ተሞክሮ(life experience) ውጤት ነኝ ፤ ስለሆነም ሁለትና ሦስት ወይም ከዚያ በላይ የሰው ባህርያትን በውስጤ ይዤ በምድር ላይ ከኖርኩ በኋላ ብሞት በኋላ በምኖረው ሕይወት የመገለጫዬ ባህርይ ማን ሊሆን ነው? " በማለት ይጠይቃል ።

□□□

በመጨረሻም " ከሥጋህ ውጭ ነፍስ ኖረ ወይም አልኖረስ ምን ያደርግልሃል? ሥጋህ እዚህ ምድር ላይ ለትል ተሰጥቶ የሚበሰብስና የሚጠፋ ከሆነ ነፍስህ ያለ ሥጋ ምን ዓይነት ደስታና እርካታ ለማግኘት እንደምትል ማሰቡ ግራ ይገባል? " ብሏል ።

□□□

እንግዲህ እንዲህ እየጠየቅን ስንሄድ ፈላስፎቹ ከወደ መጨረሻው ላይ የሚስማሙበት አንድ ሃ ሳብ " ዘላለማዊ ሕይወትን የምንመኘው ሕይወትን ስለአፈቀርናት ሳይሆን ሞትን ሰለምንፈራው ነው ። ሰው ለሞት ማሸነፍያ የፈጠረው ብቸኛ መድኃኒት ዘላለማዊ ሕይወት ነውና " ይላሉ ። ...

ይቀጥላል...

@filsfina @filsfina

ዘላለማዊነት በፍልስፍና ሲመዘን

/ ክፍል ፫ /

□□□□

ብዙውን ጊዜ በሕይወት እንሰለቻለን ። ሕይወት ከጭንቀቷ ፣ ከሕመሟ ፣ ግራ ከማጋቧቷና ከሐሳቧ...ጋር በሌላ ዓለም ሊኖሯት የምትናፈቅ አይደለችም፤ አሊያም ጁሊየስ ቄሳር እንዳለው " ሰው ከሚገባው በላይ ረዥም ዕድሜውን ይኖራል " ።

□□□

በጥቅሉ የፈላስፎች ሐሳብ እንግዲህ " የትኛውም እንስሳ አንዱ እንስሳ በሌላኛው ሲበላ ወይም ሲሞት በማየት ለጊዜው ከሚፈጠረው ቅፅበታዊ ድንጋጤ ውጪ ሞትን አያውቅም፤ ስለዚህም ለየትኛውም እንስሳ ሞት ትርጉም የለውም ። ወደ ሰው ልጅ ስንመጣ ግን ሰው ማሰብን ያዳበረ ፍጡር ስለሆነ ሞት እንዳለበት ተረዳ ፤ ስለዚህም ለአእምሮው እረፍትን ለመስጠት ዘላለማዊ ሕይወትን ፈጠረ " የሚል ነው ። ታላቁ ደራሲ ቪክቶር ሁጎስ ፦

" የተወለድክ ቀን ለመሞት ተረግመሃል " ብሎን የለም ። የሰው ልጅ ለመሞት መረገሙን በማወቁ ደግሞ በውስጡ ፍርሃት አነገሰ ። እንግዲህ ፈላስፎቹ ደግሞ እዚህ ላይ ይነሱና " ሰው ሞትን በመፍራቱ ሃይማኖት ተጀመረ " ይሉናል ።

□□□

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አይነቱን አሳቢ "አንተ ሞኝ" ይለዋል ፦

" ነገር ግን ሰው ፦ ሙታን እንዴት ይነሳሉ በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል ። አንተ ሞኝ፤ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም..." (1 ኛ ቆሮ 15፥35-41)

⁞

ጠቢቡ ሰለሞን ደግሞ በመክብብ መጽሐፉ ፦ " እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ እስከፍፃሜ ድረስ የሠራውን ሥራ ሰው መርምሮ እንዲያገኝ ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው " ይላል ። (መክ 3፥11)

⁞

ዘላለማዊነትን ማሰቡ ያስጨንቃል፣ ለመሆኑ ዘላለማዊነት በራሱ ማቆምያው የት ይሆን ? !

✻ ተፈፀመ ✻

□□□

ምንጭ " ጥበብ ከጲላጦስ (4 በ 1) ቅጽ ፭ እንዲሁም Other philosopical books

ከፍልስፍና ዓለም እንዲሁም ንባብ ለሕይወት ቴሌግራም ቻናሎች ዝግጅት ክፍል

@filsfina @books4all32